# ዓለም አቀፍ የተጋሩ የወንጌል አማኝ ክርስትያኖች ሕብረት

## Global Alliance of Tigraian Evangelical Christians

## <u>የአቋም መግለጫ</u>

**ጥር 23 ቀን 2013 ዓ/ም**

ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ የኢትዬጵያ መንግስትና የግል ሚዲያዎች በትግራይ ሕዝብ ላይ በከፈቱት የተቀነባበረ የጥላቻ ዘመቻ ብዙዎች የትግራይ ተወላጆች ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ ታስረዋል፣ ከሥራ ተባረዋል፣ ለብዙ ዘመናት ከኖሩበት ስፍራ ተፈናቅለዋል፣ ንብረታቸው ተወርሷል፣ ሸቀጣ ሸቀጥ እንዳይገባ መንገዶች ተዘግተዋል፣ በትግራይ የተጀመሩ መሠረተ ልማቶች እንዳይሰሩ ተስተጓጉለዋል፣ ኢንቨስተሮች እንዳይገቡ ታግደዋል፣ባጀት ተከልክለዋል ወዘተ፡፡

ይህ አልበቃ ብሎ ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ/ም ሕግና ስርዓትን አስከብራለሁ በሚል ሰበብ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የባእድ ሀገራት ማለትም የኤርትራና የሶማሌ ጦር፣ እንድሁም የአማራ ክልል ሚሊሻና ልዩ ኃይልን ጨምሮ በአረብ ኤምሬትስ ድሮን በመደገፍ መጠነ ሰፊ፣ አውዳሚና አስከፊ ጦርነት በትግራይ ሕዝብ ላይ እየተካሔደ ይገኛል፡፡ በዚህም ብዙ ሺዎች ውድ ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ ሚሊዬኖች ተፈናቅለው ለአስከፊ ረሐብ፣ በሽታና ስደት ተጋልጠዋል፣ ሴቶች ተደፍረዋል፣ ቤቶች መንደሮች የእርሻ ቦታዎች ተቃጥለዋል፣ ፋብሪካዎችና መሠረተ ልማቶች ወድሟል፣ ንብረት ተዘርፎ ወደ ኤርትራ ተወስደዋል፣ የሐይማኖትና የታሪክ ቅርሶች ፈራርሰዋል ተዘርፋል፣ የትግራይን መሬት ተከፋፍሎ ለኤርትራ ጭምር ተሰጥቷል፤ የውኃ፣ መብራት፣ ባንክ፣ ስልክና ኢነተረኔት አገልግሎት ተከልክሎ ከሌላው ዓለም ተለይተዋል፡፡ ስለዚህም የትግራይ ህዝብና ምድር በብዙ ስቃይና በቃላት ለመግለፅ በሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ ይገኛል፡፡

በመሆኑም እኛ በዓለም ዙርያ የምንገኝ ተጋሩ የወንጌል አማኝ ክርስትያኖች (ፕሮቴስታንት) በመስባሰብ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. የኢትዮጵያ መንግሥት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነብስ አድን የሰብአዊ እርዳታ ለሕዝባችን ለማድረስ እየጠየቁ ላሉ አለም አቀፍ እና አገር በቀል ድርጅቶች ባስቸኳይ የመግቢያ በሮችን (Humanitrian Corridors) እንዲከፍት አንጠይቃለን፡፡

2. በኢትዮጵያ መንግሥት ተጋብዞ በትግራይ ምድር ሰፍሮ በሕዝባችን ላይ ሰቆቃና ውድመት እያደረሰ ያለውን ጨፍጫፊና ዘራፊውን የኤርትራ ጦር ባስቸኳይ ከምድራችን እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡

3. ይህ የዕልቂት ጦርነት ባስቸኳይ ቆሞ ለሠላምና ለድርድር ዕድል እንዲሰጥ፣ በከፍተኛ የሕዝብ ድምፅ የተመረጠው ሕጋዊው የትግራይ መንግሥት ወደ ቦታው እንዲመለስ፣ የደረሰው መጠነ ሰፊ ዕልቂትና ውድመት በነፃና ገለልተኛ አካል እንዲጣራ፣በዘራቸው ምክንያት በተለያዩ የአገሪትዋ ክፍል በየእስር ቤቱ እየማቀቁ ያሉ የትግራይ ተወላጆች እንዲፈቱና የተዘረፈ ንብረታቸው እንዲመለስ እንጠይቃለን፡፡

4. የክርስቶስ አካል የሆነቿው የኢትዩጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስትያን (ፕሮቴስታንት) ለሠላም፣ ለዕርቅ፣ ለተጎዱ፣ ለስደተኞችና ለመበለቶች፣ ለማሕበራዊ ፍትህና ለልማት መቆም ሲገባት፤ በተቃራኒ ጎራ ተሰልፋለች፡፡ ከዚህ በፊት አገሪቱ የእርስ በረስ ግጭት ውስጥ ገብታ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በቤንሻንጉልና ሌሎች አከባቢዎች ከፍተኛ ውድመትና እልቂት ሲደርስ አይታ እንዳላየች ዝምታን መምረጥዋ ይታወሳል፡፡ አሁን ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ለመጨፍጨፍና ዘርን ለማጥፋት የወጣውን ገዳይ መንግሥትና ሠራዊት በመደገፍና መርቆ በመላክ ተባባሪ ሆናለች፡፡ ይባስ ብሎም የትግራይ ሕዝብ በወራሪው የኤርትራ ሠራዊት ሲጨፈጨፍ፣ ሐብቱና ንብረቱ ሲዘረፍና ሲቃጠል፣ ሴቶች ሲደፈሩ፣ ሕፃናት ሲገደሉ፣ ሕዝብ በረሐብ ሲሰቃይና ከአገሩ ሲሰደድ አሁንም ይህች ቤተክርስትያን ተቃውሞ አለማሰማቷ እጅግ አሳዛኝና ከክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የማይጠበቅ ለወደፊትም በትግራይ ለሚሰራው የወንጌል ሥራ ዕንቅፋት የሆነ፣ "ባልንጀራህ እንደራስህ ውደድ" ማርቆስ 12፥31 የሚለውን የጌታ የእየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ትዕዛዝ የሻረና በትግራይ ሕዝብ ላይ የተፈፀመ ከባድ የታሪክ ጠባሳ መሆኑን እየገለፅን አሁኑም የወንጌላዊት ቤ/ክርስትያን እንደተቀበለችው የወንጌል አደራ ፍቅር ርህራሄና ቅን ፍርድ ያለበትን አቋም ይዛ እንድትወጣ ከፀሎት ጋር አጥብቀን እናሳስባለን፡፡

5. ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስትያን፣ ለእስልምና እምነት መሪዎችና ለሌሎች የሃይማኖት አባቶች፣ ሠላም ወዳድ የሆናችሁ ብሄር ብሄረሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የሴቶች ማሕበራት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ አክቲቪስቶች ወዘተ የእስካሁን ዝምታችሁ የሚያሳዝን ቢሆንም፤ ይህ ለከፍተኛ ዕልቂትና መከራ የተጋለጠውን የትግራይን ሕዝብ ለማዳን እንደ እግዚአብሄር ቃል ከእውነትና ከቅን ፍርድ ጎን እንድትቆሙ በክርስቶስ ፍቅር እናሳስባለን፡፡

6. እሰከ ዛሬ ድረስ በፀሎት፣ ድምፅ በመሆን፣ በሞራል፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ ወዘተ ከትግራይ ሕዝብ ጎን የቆማችሁ ኢትዮጵያዊያን፣ ኤርትራዊያን፣ የሌሎች አገሮች ዜጎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ አገልጋዮች፣ አክቲቪስቶች እግዚአብሄር በርህራሄ ልባችሁን አነሳስቶ ስለአደረጋችሁት መልካም ሥራ እግዚአብሄር ይባርካችሁ እያልን ለወደፊትም በጌታ ፍቅር አብራችሁን እንደምትቆሙ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

7. በአገር ውስጥና በውጭ የምትገኘው የምንወድህ የትግራይ ሕዝባችን ሆይ እኛ በዓለም ዙሪያ የምንገኝ ተጋሩ የወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች በዚህ በምናልፍበት አሰቃቂ የጦርነት ሕይወት ውስጥ አብረን ማልቀስና ማዘን ብቻ ሳይሆን በፀሎት፣ የሕዝባችን ድምፅ በመሆን፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ ፣ በሞራልና በሚያስፈልገው ሁሉ ከጎንህ መሆናችንን እየገለፅን ምድራችንና ህዝባችን መልሶ ለመገንባትና ለማቋቋም የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡

"እግዝኣብሔርን ተስፋ አድርግ፤ በርታ፤ ልብህም ይጽና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፡፡" መዝ 27፥14

**እውነት ምን ጊዜም ያሸንፋል!!!**

## ዓለም አቀፍ የተጋሩ የወንጌል አማኝ ክርስትያኖች ሕብረት አስተባባሪ ኮሚቴ